# የጀግናው ቴዎድሮስ ወኔ ያልተለየህ፤ የበላይ ዘለቀን ሱሪ የታጠቅህ

# ህዝብ ሲታሰር ሲገደል ምን ትጠብቃለህ?

ከጌታቸው ጋረደው

መለስ ዜናዊ ግንቦት 7-1998 የተደረገውን ብሄራዊ ምርጫ በማጭበርበር አሸንፌ ያለሁ በማለት የፖለቲካ ስልጣኑን ለብቻው ጨብጦ ፈላጭና ቆራጭ የሆነው ሳያንሰው፤ እውነተኛ የምርጫው አሸናፊ የነበሩትን ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አባላትን በሀሰት ክሶ በክህደት ወንጀል አስሮ በቀጠሮ ሲያጉላላቸው ከቆየ በኋላ፤ የመጨረሻው ውሳኔ ለዛሬ የካቲት 12-1999 እንደሚሰጥ ስለገለጸ፤ በአገር ቤት ያለው ህዝብና በመላው አለም ተበታትነን የምንኖረው ኢትዮጵያዎያን ስደተኞች ይህችን ቀን እንደወላድ ሴት ቀኑን ስንቆጥር፤ በዋዜማው ሰሞን በትልልቅ ከተሞች ተገናኝተን ስንወያይ፤ በናፍቆት የጠበቅናት ቀን ስትመጣ፤ ሰብሳቢው ዳኛ ያልጠበቅነው ምክንያት በመስጠት፤ ወሽመጣችንን ቆረጠው።

አቶ ሀይሉ ሻውል ከምርጫው በፊት ይሁን ወይም በኋላ በአሜሪካ ውስጥ የተናገሩት ንግግር፤ የምርጫው ቦርድ ያወጣው የመጨረሻ ውጤት፤ እንዲሁም ምርጫውን በተ መለከተ የወጡትን ጽሁፎች ሁሉ በታወቀ ተርጓሚ ተተርጉሞ እንዲቀርብ ለየካቲት 26-1999 አዲስ ቀጠሮ ሲያዝ፤ በተጨማሪ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር አቶ ያማማቶ የዶክተር ብርሀኑን አባትና የአቶ ሀይሉ ሻውልን ልጅ አባብለው እስረኞቹ ሰሩ የተባሉትን ወንጀል አምነው የመለስን መንግስት ይቅርታ ቢጠይቁ ሊፈቱ ይችላሉ በማለት ለማግባባት ያደረጉት ጥረት ከመከሸፉ ሌላ፤ እስረኞቹ ለመፈታት ያልሰሩትን ወንጀል ሰርተናል ብለው ከመፈረም ማናቸውንም የፍርድ ውሳኔ መቀበሉን ይመርጣሉ በማለት በታሳሪዎቹ ስም ሁለቱ የሰጡት የጀግና መልስ አባትንና ልጅን ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም የሚያኮራ ነው። የአንድ ታላቅ አገር አምባሳደር አቶ ያማቶቶ መለስ ዜናዊ ምርጫውን አጭበርብሮ እንዳሸነፈ እያወቁ፤ የቅንጅት መሪዎች ችግር በፖለቲካ የሚፈታ እንጂ የፍርድ ውሳኔ የሚሰጥበት አለመሆኑን እይተረዱ የቅንጅት መሪዎች ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲጠይቁ ብሎ መገፋፋት ከአንድ አምባሳደር የማይጠበቅ ስራ ለመፈጸም መሞከራቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ነው።

የዛሬው ችሎት በአዲስ ቀጠሮ እንደሚበተን ሁላችንም የጠበቅነው ቢሆንም የተሰ ጠው ምክንያት ይህ ከዳኛው የሰማነው አልነበረም፤ አንደኛ አቶ ሀይሉ ሻውል አሜሪካ ውስጥ የተናገሩት ንግግር አዲስ የይደለም፡ሁለተኛ የምርጣው ቦርድ ስለምርጫው ውጤት እውነትም ሆነ የማጭበርበር ሰነድ እንዳለው ሁላችንን እናውቃለን፤ ሶስተኛ ምርጫውን በተመለከተ ተነገሩ ወይሞ ተጻፉ የተባሉት ጉዳዮች ለመለስ ዜናዊ ወይም ለዳኛው አስፈላጊ መሆኑን እያወቁ፤ ለምን ቀደም ብለው አላዘጋጁም፤ ወይም ተከሳሾች በጠበቆቃቸው አማካይነት አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ለምን አለተደረገም? አዲሱን ቀጠሮ ከሁለት ሳምንታት በኋላ ያደረገው ለምንድነው? ለታሳሪዎቹ አዝኖ ነው? አይደለም፤ ቀጠሮውን በአጭር ያደረገው ህዝቡን ለማዘናጋት፤ ቀጠሮው አጭር ስለሆነ እንጠብቅ እናስጨርሰው በማለት ህዝቡ እንዳያምጽ ለማታለል የተደረገ ዘዴ ነው። በየካቲት ወር መጀመሪያ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ባወጣው መግለጫ ከየካቲት 5-1999 ጀምሮ ከአንደኛ ክፍል እስከ ዩኒቬርስቲ ያሉ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ግን መለስ ዜናዊ እንዳለፈው ጊዜ በአጋአዚ ወታደሮች እንዳይገላቸው ከቤታቸው እንዳይወጡ ሲያስጠነቅቅ፤ በዚህ በተማሪዎች እርምጃ መለስ ካልተንበረከከ ሌላ እርምጃ እንደ ሚወስዱ ስለገለጹ በቀጠሮው ማጠር ሀሳባቸውን እንዳይለውጡ አደራ እንላቸዋለን።

በጥቅምት ወር መጨረሻ 1998 ቅንጅት ባወጣው መግለጫ በመላ ኢትዮጵያ ያሉ ሰራተኞች በሙሉ የስራ አድማ አድርገው ከቤታቸው እንዳይወጡ ስለአሳሰቡ መዋሸት የማይደክመው መለስ ዜናዊ በመደንገጥ፤ ይህ አድማ እንዳይደረግ የቅንጅት መሪዎችን ለምኖ ስለአልተሳካለት፤ በኢትዮጵያ የሚገኙ አምባሳደሮችን ቤት እየፈለገ የቅንጅት መሪዎች ሀሳባቸውን እንዲለውጡ እንዲያማልዱት፤ሲለምን

እነሱ የሚፈልጉትን ጉዳይ እንደሚቀበላቸው ቃል ስለገባ፤ አድማው እንዲቀር ተደረገ ከአድማው መሰረዝ በኋላ በተደረገው የመንግስትና የቅንጅት ስብሰባ፤ በበረከት ሲሞን ሰብሳቢነት አንዳች የተጨበጠ ነገር ሳያገኙ ተለያዩ። በአማላጅነት የተላኩት አምማባሳደሮች፤ የቅንጅት መሪዎች አድማውን ከሰረዙ መለስ በበኩሉ የእነሱን ጥያቄ ተቀብሎ በተግባር እንደሚያውል ቃል ገብተው ነበር፤ ግን በመጨረሻ አምባሰደሮቹ የገቡትን ቃል ማስፈጸም ቀርቶ ለሰሩት ስህተት ይቅርታ እንኳን አልጠየቁም። የቅንጅት መሪዎች የመለስን ውሸትና ማታለል እያወቁ፤ ሀሳቡን መቀበላቸው ስህተት ቢሆንም ይህንን ያደረጉት፤ ሰላምን በመፈለግ አምባሳደሮቹን ላለማስቀየም በይሉኝታ ያደረጉት ውሳኔ ነበር፤ ግን በዚህ ምክንያት የቅንጅት መሪዎች የእዳው ከፋይ በመሆን በእስር ቤት ሲማቅቁ፤ መለስ አሁንም ስልጣኑን ይዞ ለሁለተኛ ጊዜ ለማታለል የዛሬውን ቀጠሮ ለየካቲት 26-1999 አስተላልፏል፤ ሊበሉት የፈለጉትን እርኩም ጅግራ ነው ይሉታል እንደሚባለው ምሳሌ፤ መለስ ለሁለተኛ ጊዜ ማታለል በዳኛው በኩል የሰጠው ምክንያት ተቀባይ ያገኛል? የቅንጅት መሪዎች የዳኛውን ትእዛዝ ለመሻር ባይችሉም፤ አሁን በቅርቡ መለስን ለማዳከም ተማሪዎችና ጠቅላላው ህዝብ በየቀኑ እንዲያደርግ ያዘጋጁትን እቅድ በተግባር ማሳየት ሲገባቸው፤ ይህንን አስራ አምስት ቀናት ሳይጠቀሙበት ካሳለፉ፤ ሁለተኛ ስህተት መስራት ስለሆነ፤ እንዲያስቡበት አደራ እንላለን። መሪዎቻችን በእስር ቤት ቢገኙም ህዝቡ ፍላጎታቸው ስለሚገባው በአካል ባያገኛቸውም በመንፈስ ከነሱ ጋር ስለሆኑ፤ እምነታቸውን በህዝቡ ላይ ይተዉት።

አገር ቤት ያለው ህዝብ ሆነ በውጭ አገር ያለው ስደተኛ ያለበት ችግር ይህንን ዘረኛ አስከፊ አመራር ለማስወገድ ዝግጁ ሲሆን፤ ትልቁ ችግሩ የሚመራው የሚገፋፋው መሪ የለውም፤ የታሰሩት መሪዎቹ የተነሱበትን የተቀደሰ አላማ ከግቡ ለማድረስ እስራትን ሆነ ሞትን በጸጋ ለመቀበል ዝግጁ ቢሆኑም፤ በህዝቡ መካከል ስለአልሆኑ፤ እነሱን ወክሎ የሚመራን ጀግና ስለአጣን፤ የጀግናው የቴዎድሮስ ወኔ ያልተለየው፤ ወይም የበላይ ዘለቀን ሱሪ የታጠቀ ጀግና ማጣታችን፤ የጎበዝ ፈሪ አድርጎ ስለያዘን፤ ፈሪዎቹ ወኔቢሶች ሆነን ገለን ከመሞት፤ እንደ ሳዳም ሁሴን እንደ በግ እየተጎተትን እንገደላለን። በአለም የታወቅነው በድህነታችን ብቻ ሳይሆን በፈሪነትም ስንታማ እጅግ የሚያሳፍረን ነው። ባለፉሩት አስራ አምስት አመታት መለስ ዜናዊ ስንት ሺህ ህዝብ ገደለብን ስንት ጎበዝ በየደኑ በየጫካው አፈር ሆኖ ቀረ? ይህንን እየሰማን እያየን ፤ በመቃወም ፈንታ ከወያኔ መሪዎች የተረፈውን ፍርፋሪ ለመብላት አጎብድደን መለመን አንዱ ሌላውን አሳልፎ መስጠት ተግባራችን ስለሆነ፤ በመካከላችን መተማመን የለም። የኛ ታላቁ ጠላታችን ሆዳችን ስለሆነ፤ መለስ ለረጅም አመታት የገዛን ወደፊትም የሚገዛን በሆዳችን ነው።

በላይ ዘለቀ በአምስቱ አመታት የጠላት ወረራ ፋሽሽትን መግቢያና መውጪያ በማሳጣት ላደረገው ጀብዱ ስራ መሸም መሸለም ሲገባው የድካሙ ዋጋ በአጠና እንጨት ላይ መሰቀል ስለነበር፤ የሚሰቀልበት ገመድ አንገቱ ላይ ታስሮ ከመሰቀሉ በፊት። ።እትዮጵያ አገሬ ወንድ አይብቀልብሽ ብሎ ስለተራገመ፤ ከዚህ ቀን ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ በበላይ ዘለቀን ሱሪ የታጠቀ ስለጠፋ ሁላችንም የአንድ ሰው የመለስ ዜናዊ ሰለባዎች ሆነን እንኖረለን፤ ከበላይ ዘለቀ በኋላ አንድአንድ ጀግኖች የህዝቡን መብትና ነጻነት ለማስከበር ቢነሱም፤ ጀግኖችን መግደል ልማዱ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ መንግስቱ ንዋይን ሲሰቅል፤ ራሳቸውን የገደሉ ጀግኖች አስከሬን ስቅሎ መቀጣጫ አደረጋቸው፤ ይህ ሁሉ አሳፋሪ ነገር የተፈጸመው ለአንድ ሰው ጥቅም እንደነበረ ብናስታውስም፤ ዛሬም ለመለስ ዜናዊ ጥቅም እርስ በእርሳችን እየተገዳደልን ስንኖር፤ የጋራ ጠላታችንን ለመግደል የፈራው የመከላከያ ሰራዊታችን የገበሬውን የግብር ገንዘብ እየበላ የራሱን ህዝብ የሚያስጨርሰው ሳያንሰው፤ መለስ ዜናዊ የአሜሪካ ቅጥረኛ በመሆን ወደሱማሊያ ስለላከው በማያገባው ጦርነት እየሞተ ቤተ ሰቡን ያለአባወራ አስቀርቷል።

የዚህ ጽሁፍ መልእክት የራሳችንን ስህተት እንድናርም፤ ለማስታወስ ብቻ ሳይሆን የቅንጅት መሪዎቻችን መጪውን አስራ አምስት ቀናት ያሰቡትን እቅድ በተግባር እንዲያውሉ፤ ባለፈው የሰሩት ስህተት እንዳይደገም ለማሳሰብ ነው። በእነዚህ አስራ

አምስት ቀናት ለምንወስደው እርምጃ መለስ ዜናዊ በወታደር ያስገድለናል ብለን እንፍራ፤ እኛ እንደመለስ መትረየስና አዳፍኔ መሳሪያ ባይኖረንም ከመለስ የበለጠ ሀይላችን አንድነትና ህብረት ስለሆነ፤ የማታ የማታ አሸናፊዎች ስለሆንን ተባብረን እንነሳ። ለመለስ ጥይትና ቦንብ አያስፈልገንም፤ ምክንያቱም ሰለሚፈራ ተደብቆ ስለሚኖር አናገኘውም፤ እሱ አጥብቆ የሚፈራው ሰላማዊ ሰልፍን ብቻ ነው። በ1997 በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ በአዲስ አበባ ከሶስት ሚሊዮን ህዝብ የበለጠ ለሰልፍ ስለወጣ መለስ ፈርቶ ቤተሰቡን ይዞ ደብረ ዘይት አየር ሀይል ካምፕ ውስጥ ተደብቆ እንደኖረው፤ አሁንም ይህንን ሰልፍ ብናደርግ በአጥር ጊዜ አገር ለቆ ይሸሻል ወይም በእርጥብ ሱሪው ልንይዘው እንችላለን። ይህንን ማድረግ የሚገባን ከሚቀጥለው ቀጠሮ በፊት በሚመጡት አስራ አምስት ቀናት ማድረግ ሲገባን ታላቁ ችግራችን መሪ ማግኘት ስለሆነ በዚህ ቀውጢ ሰአት አንድ ጎበዝ እናገኝ ይሆናል፤ ገበዝን የሚፈጥር ጊዜና ሁኔታ ስለሆኑ የአበበ አረጋይን የበላይ ዘለቀንቍ የገረሱ ዱኩን ጋሻ ያነሱ ጀግኖችን የኢትዮጵያ አምላክ እንዲልክልን እንማጸነዋለን።

ይህንን ጽሁፍ የሚያነቡ ዜና አሰራጮች ጽሁፉን እንዲያሰራጩልን እየለመናቸው ኢንተርኔት አገር ቤት የተከለከለ ስለሆነ ራዲዮ ጣቢዎች ቢያስተላልፉልን ብሄራዊ ግዳጃቸውን ስለፈጸሙ በአድማጮች ስም ከፍ ያለ ምስጋናችንን እናቀርባለን።
ከላይ የተጠቀሰውን እቅድ በስራ ካዋልን፤ የካቲት 26-1999 ከቅንጅት መሪዎቻችን ጋር እናከብራለን፤ ይህንን እድል ካልተጠቀምንበት የምንከፍለው ዋጋ ከፍ ያለ ሲሆን የቅንጅት መሪዎችም የፕሮፌሶር አስራት ወልደየስ እድል ስለሚጠብ ቃቸው፤ የኢትዮጵያ አምላክ ከኛ አደጋ ይሰውረን።

ፍራንክፉርት የካቲት 12-19999 (19.02.07 )